የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ

# ፌደራል ነጋሪት ጋዜጣ

# FEDERAL NEGARIT GAZETTE

OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA

ሃያ አንደኛ ዓመት ቁጥር ፴፩
አዲስ አበባ የካቲት ፲ ቀን ፪ሺ፯ ዓ.ም

በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ጠባቂነት የወጣ

21st Year No.31
ADDIS ABABA 17th February, 2015

ማውጫ

ደንብ ቁጥር ፫፻፵፩/፪ሺ፯ ዓ.ም

የቁም እንስሳት ግብይት የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ……………………………ገጽ ፰ሺ፩፻፳፮

CONTENTS

Regulation No. 341/2015

Live Animals Marketing Council of Ministers Regulation……………………………Page 8126

የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር ፫፻፵፩/፪ሺ፯

## ስለቁም እንስሳት ግብይት የወጣ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ

የሚኒስትሮች ምክር ቤት የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ አስፈጻሚ አካላትን ሥልጣንና ተግባር ለመወሰን በወጣው አዋጅ ቁጥር ፮፻፺፩/፪ሺ፫ አንቀጽ ፭ እና በቁም እንስሳት ግብይት አዋጅ ቁጥር ፰፻፲፱/፪ሺ፮ አንቀጽ ፲፰ (፩) መሠረት ይህንን ደንብ አውጥቷል፡፡

### ክፍል አንድ

### ጠቅላላ

**፩. አጭር ርዕስ**

ይህ ደንብ "የቁም እንስሳት ግብይት የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር ፫፻፵፩/፪ሺ፯" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

**፪. ትርጓሜ**

በዚህ ደንብ ውስጥ የቃሉ አገባብ ሌላ ትርጓሜ የሚያሰጠው ካልሆነ በስተቀር፡-

፩/ "አዋጅ" ማለት የቁም እንስሳት ግብይት አዋጅ ቁጥር ፰፻፲፱/፪ሺ፮ ነው፤

፪/ በአዋጁ አንቀጽ ፪ የተሰጠ ትርጓሜ ተፈጻሚ ይሆናል፤

COUNCIL OF MINISTERS REGULATION No. 341/2015

## COUNCIL OF MINISTERS REGULATION TO PROVIDE FOR LIVE ANIMALS MARKETING

This Regulation is issued by the Council of Ministers pursuant to Article 5 of the Definition of Powers and Duties of the Executive Organs of the Federal Democratic Republic of Ethiopia Proclamation No. 691/2010 and Article 18 (1) of the Live Animals Marketing Proclamation No. 819/2014.

### PART ONE

### GENERAL

1. **Short Title**

This Regulation may be cited as the "Live Animals Marketing Council of Ministers Regulation No.341/2015".

2. **Definitions**

In this Regulation unless the context otherwise requires:

1/"Proclamation" means the Live animals Marketing Proclamation No. 819/2014;

2/ definitions provided for under Article 2 of the Proclamation shall be applicable;

ያንዱ ዋጋ
Unit Price 20.90

ነጋሪት ጋዜጣ ፖ.ሣ.ቁ. ፹ሺ፩
Negarit G. P.O.Box 80001

፫/ በአዋጁ አንቀጽ ፪ (፩) ለቁም እንስሳት የተሰጠው ትርጉም የጋማ ከብትንም ይጨምራል፤

፬/ "ማቆያ ጣቢያ" ማለት ከዳልጋ ከብት ውጭ የሆኑ የቁም እንስሳት ከመጀመሪያ ደረጃ የቁም እንስሳት የግብይት ማዕከል ተገዝተው ወደ ሁለተኛ ደረጃ የቁም እንስሳት ግብይት ማዕከል ከመጓጓዛቸው በፊት የሚቆዩበት የተከለለ ቦታ ነው፡፡

## ክፍል ሁለት
## ስለቁም እንስሳት የግብይት ማዕከላት

**፫. የግብይት ማዕከላት ብዛትና ሥርጭት**

አግባብ ያለው የክልል አካል በቁም እንስሳት ግብይት ሥልጣን ከተሰጣቸው ሌሎች አካላት ጋር በመመካከር የቁም እንስሳት የግብይት ማዕከላት በአርቢዎች አካባቢ እንዲደራጁ ያደርጋል፣ ብዛትና ስርጭታቸውንም ይወስናል፡፡

**፬.የመጀመሪያ ደረጃ ግብይት ማዕከላትን ስለመሰየም**

፩/ አግባብ ያለው የክልል አካል በቁም እንስሳት ግብይት ሥልጣን ከተሰጣቸው ሌሎች አካላት ጋር በመመካከር የመጀመሪያ ደረጃ የቁም እንስሳት የግብይት ማዕከላትን ሲሰይም፣ ብዛትና ስርጭት ሲወስን የሚከተሉትን መስፈርቶች ከግምት ማስገባት ይኖርበታል፦

ሀ) ለቁም እንስሳት አርቢዎች ያላቸውን ቀረቤታ፤

ለ) ለተሽከርካሪዎች ተደራሽነት ያላቸው አመቺነት፤

ሐ) ለተጠቃሚዎች ያላቸው ቀረቤታ፤

መ) ለውሀና መኖ አቅርቦት ያለውን አመቺነት፤

ሠ) የተለያዩ የቁም እንስሳት ዝርያዎችን፣ እድሜ እና ዓይነት በመለየት ለመገበያየት ያላቸውን አመቺነት፤

3/ definition provided for live animal under Article 2 (1) of the Proclamation shall include draft animals;

4/ "waiting center" means an enclosed place used to stay live animals, except cattle, for a limited period of time after their purchase from first level live animals market center until they are transport to second level live animals market center.

## PART TWO
## LIVE ANIMLAS MARKETING CENTERS

**3. Number and Distribution of Market Centers**

The appropriate regional organ shall, in consultation with others bodies having the power to regulate live animals marketing, organize live animals marketing centers around the breeders and determine their number and distribution.

**4. Designating First Level Market Center**

1/ The appropriate regional organ shall, in consultation with others bodies having the power to regulate live animals marketing, when designating the first level live animals market centers and determining their number and distribution, consider the following particulars:

a) their proximity to breeders;

b) their convenience for access by vehicles;

c) their proximity to users;

d) their convenience for access to feeds and water supply;

e) their convenience for marketing of different breeds, age and types of live animals;

ረ) ለቁም እንስሳት የጤና ጥበቃ ሥራዎች፣ የደረጃ ምደባና የጨረታ ግብይት ለማካሄድ ያላቸውን አመቺነት፣

ሰ) ሚኒስቴሩ የሚያወጣውን መመሪያ በመከተል ከመኖሪያ አካባቢዎች፣ ከትምህርት ቤቶች፣ ከጤና ተቋማት፣ ከእምነት እና ከሌሎች ማህበራዊ አገልግሎት ሰጪ ተቋማት በበቂ ርቀት ላይ መገኘታቸውን፣

ሸ) የገበያ ማዕከላቱን ለማስፋፋት ያላቸ ውን አመቺነት፣እና

ቀ) ለቁም እንስሳት ግብይት ተሳታፊዎች መሠረታዊ ፍላጎት ማሟያ የአገልግሎት መስጫ ተቋማት በአካባቢው መኖራ ቸው፡፡

፪/ የግብይት ማዕከል ለአጎራባች ወረዳዎች እና ቀበሌዎች የሚያገለግል ከሆነ አሰያየሙ አግባብ ያለው የክልል አካል ከአጎራባች ወረዳዎቹ እና ቀበሌዎቹ አስተዳደር አካላት ጋር በጋራ የሚወስኑት ይሆናል፡፡

፫/ የገበያ ማዕከላቱን እንዲያስተዳድር ሥልጣን የተሰጠው የወረዳ ወይም የቀበሌ አካል የግብይት ማዕከሉ በከተማ ክልል የሚገኝ ከሆነ ካርታና ፕላን ወይም በገጠር የሚገኝ ከሆነ ደግሞ የመሬት ይዞታ ማረጋገጫ ደብተር እንዲኖረው ያደርጋል፡፡

፭. **<u>የመጀመሪያ ደረጃ የቁም እንስሳት ግብይት ማዕከል ማሟላት ያለበት መስፈርት</u>**

የመጀመሪያ ደረጃ የቁም እንስሳት ግብይት ማዕከል ቦታ ስፋት እንደ አካባቢው የቁም እንስሳት እና የመሬት አቅርቦት የሚወሰን ሆኖ አደረጃጀቱ የሚከተሉትን መስፈርቶች የሚያሟላ መሆን አለበት፦

፩/ ቢያንስ ከ፭ሺ ሜትር ካሬ ስፋት ቦታ ያለው፤

f) their convenience for access of live animals health control services; standardizing and marketing through auction;

g) following the directive issued by the Ministry, their location in adequate distance from residential areas, schools, health facilities, religious institutions and other social service providing institutions;

h) their convenience for the expansion of the market capacity; and

i) their convenience for access to institutions engaged in provision of basic needs for live animals market actors.

2/ If the market center is expected to provide service to neighboring Woredas' and Kebeles', its designation shall be determined by appropriate regional organ jointly with neighboring Woredas' and Kebeles'.

3/ The competent wereda or kebele body authorized to administer the market center shall cause the center to obtain map and site plan if the center is located within town or certificate of possession of land if the center is located in a rural area.

5. **<u>Criteria to be met by the First Level Live Animal Market Centers</u>**

The widths of the first level live animals marketing center shall be determined based on the availability of land and supply of animal in the locality and its organization shall fulfill the following criteria:

1/ have an area with at least 5000 meter square;

፪/ በአካባቢው የሚገኝ ቁሳቁስን በመጠቀም የተገነባ አጥር ያለው፤

፫/ የገበያ መረጃ ሰሌዳን፣ መጫኛ እና ማራገፊያ መደላድል፣ የደረቅ ቆሻሻ ማቃጠያ እና የፍሳሽ ቆሻሻ ማስወገጃ ያለው፤

፬/ ለግብይት ተሳታፊዎች የሚያገለግል የጋራ መገልገያ መሣሪያዎች እና የመጸዳጃ ቤት ያለው፤

፭/ የተለያዩ ዓይነት የቁም እንስሳት ማስተናገድ እንዲችል የተከፋፈለ ቦታ ያለው፤

፮/ ለቁም እንስሳት በቂ ውሃ፣ መኖ፣ ህክምና አገልግሎት መስጫ ያለው እና በጤና ችግር ምክንያት ለሚገለሉ የቁም እንስሳት ማግለያ ቦታ ያለው፤ እና

፯/ ንጽሕናው የተጠበቀና ለመረጃ አገልግሎት የተመቻቸ፡፡

**፮. የሁለተኛ ደረጃ ግብይት ማዕከላትን ስለመሰየም**

፩/ አግባብ ያለው አካል የሁለተኛ ደረጃ የቁም እንስሳት የግብይት ማዕከላትን ሲሰይምና ብዛትና ስርጭት ሲወስን የሚከተሉትን መስፈርቶች ከግምት ማስገባት ይኖርበታል፡

ሀ) በዚህ ደንብ አንቀጽ ፬ (፩) (ለ)፣ (መ)፣ (ሠ)፣ (ረ)፣ (ሰ)፣ (ሸ) እና (ቀ) የተገለፁት መስፈርቶች መሟላታቸውን፣

ለ) ለቁም እንስሳት አድላቢዎች ያላቸውን ቀረቤታ፤

ሐ) ለኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጂ መረብ አገልግሎት ያላቸውን አመቺነት፤

መ) የኤሌትሪክ ኃይል አቅርቦት አገልግሎት ለማግኘት ያላቸውን አመቺነት፡፡

፪/ የግብይት ማዕከሉ ለአጎራባች ወረዳዎች ወይም ቀበሌዎች የሚያገለግል ከሆነ አደረጃጀቱ አግባብ ባለው የክልል አካልና

2/ have a fence built of local materials;

3/ have facilities such as market information board, loading and unloading facilities, solid west burning and liquid waste sewerage facilities;

4/ have common facilities and toilets for market actors;

5/ have a partition to accommodate different types of animals;

6/ have adequate facilities to provided feed, water and health service for animals and isolation places for animals identified to have health problem; and

7/ be clean and convenient for information service.

**6. Designating Second Level Market Center**

1/ The appropriate organ shall, in consultation with other bodies having the power to regulate live animals marketing when designating the second level live animals market centers and determining their number and distribution, consider the following particulars:

a) the fulfillment of particulars specified under Article 4 (1) (b), (d), (e), (f), (g), (h) and (j) of this Regulation;

b) their proximity to feedlot operators;

c) their convenience for information technology network service;

d) their convenience for supply of power.

2/ If the market center is to provide service to neighboring Woredas' or Kebeles', its organization shall jointly be determined by

የአጎራባች ወረዳዎቹ ወይም ቀበሌዎቹ አግባብ ካላቸው አካላት ጋር በጋራ ይወሰናል፡፡

፫/ የገበያ ማዕከላቱን የሚያስተዳድረው አግባብ ያለው አካል የግብይት ማዕከሉ በከተማ ክልል የሚገኝ ከሆነ ካርታና ፕላን ወይም በገጠር የሚገኝ ከሆነ ደግሞ የመሬት ይዞታ ማረጋገጫ ደብተር እንዲኖረው ያደርጋል፡፡

## ፯. የሁለተኛ ደረጃ የቁም እንስሳት ግብይት ማዕከል ማሟላት ያለበት መስፈርት

የሁለተኛ ደረጃ የቁም እንስሳት ግብይት ማዕከል ቦታ ስፋት እንደ አካባቢው የእንስሳት እና የመሬት አቅርቦት የሚወሰን ሆኖ አደረጃጀቱ የሚከተሉትን መስፈርቶች የሚያሟላ መሆን አለበት፡-

፩/ በዚህ ደንብ አንቀጽ ፭ (፫)፣ (፬)፣ (፭) እና (፮) የተገለፁት መስፈርቶች፤

፪/ ቢያንስ ፳ሺ ሜትር ካሬ ስፋት ቦታ ያለው፤

፫/ ዙሪያውን በግንብ ወይም በሽቦ በአስተማማኝ ሁኔታ የታጠረ አጥር ያለው፤

፬/ የተለያዩ ዓይነት የቁም እንስሳት ማስተናገድ እንዲችል የተከፋፈለ ቦታ ያለው፤

፭/ የግብይት ተሳታፊ ለሆኑት ኅብረት ስራ ማህበራት፣ አርቢዎች እና አድላቢዎች የቁም እንስሳት መገበያያ ተሸንሽኖ የታጠረ ቦታ ያለው፤

፮/ በግብይት ማዕከሉ በባለቤትነት የተያዘ በሥነ ልክ ኢንስቲትዩት የተመሰከረለት የቁም እንስሳት ሚዛን ያለው፤ እና

፯/ የተሟላ የውሀና የመብራት አቅርቦት፣ የመገናኛ መሰረተ ልማት፣ የጥበቃ ማማ እና ግብይት ማካሄጃ ቢሮ ያለው፡፡

## ፰. የግብይት ማዕከላት አስተዳደር

፩/ የመጀመሪያና የሁለተኛ ደረጃ የቁም እንስሳት ግብይት ማዕከላት፡-

appropriate regional organ, the neighboring Woredas' or Kebeles'.

3/ The competent wereda or kebele body authorized to administer the market center shall cause the center to obtain map and site plan if the center is located within town or certificate of possession of land if the center is located in a rural area.

## 7. Criteria to be met by the Second Level Live Animal Market Centers

The widths of the second level live animals marketing center shall be determined based on the availability of land and supply of animal in the locality and its organization shall fulfill the following criteria:

1/ those specified under Article 5 (3), (4), (5) and (6) of of this Regulation;

2/ have an area of at least 20,000 meter square;

3/ have a fence built of block or wire;

4/ have a partition to accommodate different types of animals;

5/ have space partitioned and allocated for market actors' such as cooperative union, breeder, feedlot operator for marketing live animals;

6/ have live animals weighing scale owned by the center and certified by the Ethiopian Meteorological Institute;

7/ have adequate water and power supply, communication infrastructure, guarding quarter and marketing offices.

## 8. Administration of Market Centers

1/ The first or second level live market centers shall be administered by:

ሀ) ከከተማ ክልል ውጭ የተደራጀ ከሆነ የግብይት ማዕከሉ በሚገኝበት አካባቢ ያለው አግባብነት ያለው አካል ወይም ለዚህ ተግባር ስልጣን የተሰጠው አካል የግብይት ማዕከላቱን ያስተዳድራል፤

ለ) በከተማ ክልል ውስጥ ከሆኑ ግን የከተማው ማዘጋጃ ቤት፣ አግባብነት ያለው አካል ወይም ለዚህ ተግባር ስልጣን የተሰጠው አካል የግብይት ማዕከላቱን ያስተዳድራል፡፡

፪/ ግብይት ማዕከላትን ለማስተዳደር ስልጣን የተሰጠው አካል፡-

ሀ) በቁም እንስሳት ግብይት ላይ አሉታዊ ተጽእኖ ከሚያሳድሩ የአካባቢው ሁኔታዎች ነጻ እንዲሆኑ ተገቢውን እርምጃ የመውሰድ፤

ለ) ለግብይት ሂደት የሚጠየቀው የአገልግሎት ክፍያ ከሚሰጠው አገልግሎት ጋር ተመጣጣኝ እንዲሆን የማድረግ፤

ሐ) ለግብይቱ መቀላጠፍና መሳለጥ የሚያገለግሉ መሰረተ ልማቶችን የማደራጀትና የማሟላት፤

መ) የገበያውን የዕለት ተዕለት የግብይት ሂደት፣ የቁም እንስሳቱን ጤና፣ የፀጥታ ሁኔታ እንዲሁም ተያያዥ የግብይት እንቅስቃሴ የሚከታተልና የሚቆጣጠር ሠራተኛ በበቂ ሁኔታ እንዲመደብና እንዲሟላ የማድረግ፤

ሠ) አርቢዎች፣ ህብረት ስራ ማህበራት፣ አድላቢዎች እንደ ግብይት ማዕከሉ ስፋት በሁለተኛ ደረጃ የቁም እንስሳት ግብይት ማዕከላት መሸጫ ቦታ እንዲኖራቸው የማድረግ፤

a) appropriate organ located around the center or the competent authority of the locality authorized to administer it, if it is situated outside the urban area;

b) municipal office, appropriate organ or body authorized to administer center if it is located within the urban center.

2/ The body authorized to administer the market centers shall have powers and duties to:

a) take measure necessary to make free the area from factors that negatively affect the live animals market;

b) maintain proportionality of service charge with that of the service rendered;

c) organize and fulfill infrastructures necessary that enable efficient and effective implementation of the said market.

d) assign and fulfill a responsible personnel to follow up and control the day to day marketing process, the health of live animals, security and other related marketing activities;

e) allocate sales plot to breeders, cooperative unions, feedlot operators in the second level live animals market center, based on the size of the center;

ረ) አርቢዎች፣ ህብረት ስራ ማህበራት፣ አድላቢዎች በሁለተኛ ደረጃ የቁም እንስሳት ግብይት ማዕከላት ያገኙትን መሸጫ ቦታ በተገቢው ሁኔታ አደራጅተው እንዲይዙና ለአገልግሎቱ ተመጣጣኝ ክፍያ እንዲከፍሉ የማድረግ፣

ሰ) በሁለተኛ ደረጃ የቁም እንስሳት ግብይት ማዕከላት የቁም እንስሳትን በወካይ ናሙና መሰረት የሚሸጥ የግብይት ተዋናይ ለገበያ ያቀረባቸውን የቁም እንስሳት ቁጥር በማድለቢያው ወይም በማቆያ ጣቢያው ስለመኖራቸው የማረጋገጥ፣

ሸ) በሁለተኛ ደረጃ የቁም እንስሳት ግብይት ማዕከላት በወካይ ናሙና መሰረት የሚፈፀም ግብይት በጽሁፍ ውል መፈፀሙን የማረጋገጥ እና የግብይት ተቆጣጣሪው ካረጋገጠ በኋላ የማጓጓዣ የምስክር ወረቀት የመስጠት፣ ወይም የቁም እንስሳቱን ከማድለቢያ ወይም ከማቆያ ጣቢያ እንዲረከብ የማድረግ፣

ቀ) በሁለተኛ ደረጃ የቁም እንስሳት ግብይት ማዕከላት ግብይት በድርድር ወይም በጨረታ ሲካሄድ የመቆጣጠር፣ ሥልጣንና ተግባራት ይኖሩታል፡፡

፫/ የመጀመሪያና የሁለተኛ ደረጃ የቁም እንስሳት ግብይት ማዕከላት አደረጃጀት እና አሠራር እንዲሁም ግብይት ማዕከላትን በመከለል እና በመሰየም የማሳወቂያ ጊዜ ገደብ ሚኒስቴሩ በሚያወጣው ዝርዝር መመሪያ ይወሰናል፡፡

f) cause breeders, cooperative unions, feedlot operators to handle the sales plot in an organized manner and to pay service fee proportional to service they get;

g) ensure the availability of the number of animals in feedlot operation center or animal keeping center if the animal is supplied to second level market based on the representative sample;

h) ensure that the purchase of representative sample at second level live animals market is conducted by written agreement and after being approved by the exchange controller issue transportation certificate or allow delivery to be made at feedlot or keeping center;

i) control dealing or auction of live animals at the second level live animal market center.

3/ The organization and operation of the first and second level live animals market centers and the limit of time for notification of market centers upon delineation and designation shall be determined by regulation to be issued by the Ministry.

**፱. የግብይት ቀንና ሰዓት**

፩/ በመጀመሪያ ደረጃ የቁም እንስሳት ግብይት ማዕከላት ግብይት የሚካሄድበት ቀንና ሰዓት የአካባቢውን ተጨባጭ ሁኔታ ግምት ውስጥ በማስገባት የግብይት ማዕከላቱን በሚያስተዳድረው አካል የሚወሰን ይሆናል፡፡

፪/ በሁለተኛ ደረጃ የቁም እንስሳት ግብይት ማዕከላት ግብይት የሚካሄደው ግብይት በሚኖርበት በማንኛውም ቀንና ሰዓት ይሆናል፡፡

**፲. በመጀመሪያ ደረጃ የቁም እንስሳት ግብይት ማዕከል የሚፈጸም የግብይት ሥርዓት**

፩/ የቁም እንስሳት ግብይት ተሳታፊ በአንድ የመጀመሪያ ደረጃ ግብይት ማዕከል እራሱ ወይም በሰነዶች ማረጋገጫና ምዝገባ አካል የተረጋገጠና የተመዘገበ ውክልና ሥልጣን እና የጸና ንግድ ፈቃድ ባለው በአንድ ሕጋዊ ወኪል ብቻ መገበያየት ይኖርበታል፡፡

፪/ ወደ መጀመሪያ ደረጃ የቁም እንስሳት ግብይት ማዕከል ቀርበው ያልተሸጡ የቁም እንስሳት በግብይት ማዕከሉ ተቆጣጣሪ ከተረጋገጠ በኋላ ምንም ዓይነት የአገልግሎት ክፍያ ሳይጠየቅባቸው ወደ መጡበት ይመለሳሉ።

፫/ ሚኒስቴሩ በሚያወጣው መመሪያ መሠረት በመጀመሪያ ደረጃ የቁም እንስሳት ግብይት ማዕከል የተፈፀመ ግብይት ሕጋዊ ሥርዓቱን የተከተለ ስለመሆኑ በግብይት ተቆጣጣሪው ከተረጋገጠ በኋላ የቁም እንስሳት የማጓጓዣ ፈቃድ ይሰጣል፡፡

**፲፩. በሁለተኛ ደረጃ የቁም እንስሳት ግብይት ማዕከል የሚፈጸም የግብይት ሥርዓት**

፩/ የቁም እንስሳት ግብይት ተሳታፊ በሁለተኛ ደረጃ ግብይት ማዕከል እራሱ ወይም በሰነዶች ማረጋገጫና ምዝገባ አካል የተረጋገጠና የተመዘገበ ውክልና ሥልጣን

**9. Date and Time of Marketing**

1/ The date and time of marketing of live animals at the first level live animals market center shall be determined by the body authorized to administer the center by taking into account the practical situation of the area.

2/ The date and time of marketing of live animals at the second level live animals market center shall be at any date and time where there is marketing.

**10. Process of Marketing at First Level Live Animals Marketing Center**

1/ A live animal market actor at any first level live animal market center shall conduct the marketing by himself or by only a single agent whose power of agency is authenticated and registered by a notary and who has a valid business license.

2/ Live animals supplied to first level live animal market center and not sold shall be returned back to where they came from upon approval by market center controller without paying any service fee.

3/ A transporting permit to live animals marketed at first level live animals market center shall be issued upon approval by the market controller that the purchase was conducted in conformity with the marketing procedure provided for in the directives issued by the Ministry.

**11. Process of Marketing at Second Level Live Animals Marketing Center**

1/ A live animal market actor at any second level live animal market center shall conduct the marketing by himself or by only a single agent whose power of agency is authenticated and

እና የጸና ንግድ ፈቃድ ባለው በአንድ ሕጋዊ ወኪል ብቻ መገበያየት ይኖርበታል፡፡

፪/ ከፍተኛ ቁጥር ያላቸውን የቁም እንስሳት ለሁለተኛ ደረጃ ግብይት ማዕከል የሚያቀርብ አርቢ፣ አድላቢ ወይም የኅብረት ሥራ ማህበር ሁሉንም የቁም እንስሳት ወደ ግብይት ማዕከላት ማምጣት ሳያስፈልግ የቁም እንስሳቱን ናሙና ወይም ኤሌክትሮኒክስ ማስረጃ በማቅረብ ግብይት መፈፀም ይችላል፡፡ ዝርዝር አፈጻጸሙ ሚኒስቴሩ በሚያወጣው መመሪያ ይወሰናል፡፡

፫/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፪) መሰረት የተፈፀመ የቁም እንስሳት ግብይት ሕጋዊነት በግብይት ማዕከሉ ተቆጣጣሪ ከተረጋገጠ በኋላ ተቆጣጣሪው በሚሰጠው ማረጋገጫ መሠረት የእንስሳቱ ርክክብ በማድለቢያው ጣቢያ የሚፈጸም ይሆናል፡፡

፬/ አግባብነት ያለው አካል እንደ አስፈላጊነቱ በተመረጡ አካባቢዎች በኤሌክትሮኒክስ ሥርዓት የሚታገዝ የሁለተኛ ደረጃ የቁም እንስሳት የግብይት ማዕከላት ያደራጃል፡፡ ዝርዝር አፈጻጸሙ ሚኒስቴሩ በሚያወጣው መመሪያ ይወሰናል፡፡

፭/ ሚኒስቴሩ በሚያወጣው መመሪያ መሠረት በሁለተኛ ደረጃ የቁም እንስሳት ግብይት ማዕከል የተፈፀመ ግብይት ሕጋዊ ሥርዓቱን የተከተለ ስለመሆኑ በግብይት ተቆጣጣሪው ከተረጋገጠ በኋላ የቁም እንስሳት የማጓጓዝ ፈቃድ ይሰጣል፡፡

registered by a notary and who has a valid business license.

2/ A breeder, feedlot operator or cooperative union supplying large number of live animals to market, may conduct marketing by presenting sample of the live animals or electronic evidence of animals without the need to bring all the animals to market center. The detail shall be regulated by directive to be issued by the Ministry.

3/ The legality of live animals market conducted at market center pursuant to sub-article (2) of this Article shall be approved by market center controller and delivery shall be conducted at feedlot station based on the document issued by the controller.

4/ The appropriate organ shall, as may be necessary, organize in selected area a second level live animal market center supported by electronics system. The detail shall be regulated by directive to be issued by the Ministry.

5/ A transporting permit to live animals marketed at second level live animals market center shall be issued upon approval by the market controller that the purchase was conducted in conformity with the marketing procedure provided for in the directives issued by the Ministry.

## ክፍል ሶስት

## የቁም እንስሳት ግብይት ተሳታፊዎች መብቶችና ግዴታዎች

**፲፪. የወል ግዴታዎች**

ማንኛውም የግብይት ተሳታፊ፡-

፩/ ከመጀመሪያ እና ከሁለተኛ ደረጃ የቁም እንስሳት ግብይት ማዕከላት ወይም ከማድለቢያ ጣቢያ የተገዙ የቁም እንስሳትን ከ፶ ኪ.ሜ በላይ በእግር ማጓጓዝ የለበትም፤

፪/ ከመጀመሪያ እና ከሁለተኛ ደረጃ የቁም እንስሳት ግብይት ማዕከላት ወይም ከማድለቢያ ጣቢያ የተገዙ የቁም እንስሳትን በእግርም ሆነ በተሽከርካሪ ከ፰ ሰዓት በላይ ያለእረፍት ማጓጓዝ የለበትም፤

፫/ በጉዞ ወቅት ለቁም እንስሳቱ መኖ፣ ውሃና አስፈላጊ እንክብካቤ ማድረግ አለበት፤

፬/ በእይታ ከሚለዩ ጉዳቶችና በሽታዎች ነፃ የሆነ የቁም እንስሳ ለገበያ ማቅረብ አለበት፤

፭/ በቁም እንስሳት ግብይት እና በጤና ቁጥጥር ላይ አሳሳች ድርጊት ከመፈጸም መቆጠብ አለበት፤

፮/ ከሸማች በስተቀር የቁም እንስሳትን ከመጀመሪያ እና ከሁለተኛ ደረጃ የቁም እንስሳት ግብይት ማዕከላት ወይም ከማድለቢያ ጣቢያ በመግዛት ሲያጓጉዝ በማጓጓዣ ፈቃድ ላይ የተገለጹት የቁም እንስሳት አይነትና ብዛት ትክክል መሆኑን፣ በወቅቱና በአግባቡ ወደ መዳረሻ ስፍራ ስለማድረሱ የሚገልጽ ማረጋገጫ አግባብ ካለው አካል ማግኘት ይኖርበታል፡፡

**፲፫. የአድላቢ ግዴታዎች**

የአዋጁ አንቀጽ ፲ ድንጋጌ እንደተጠበቀ ሆኖ ማንኛውም በቁም እንስሳት ግብይት ላይ የተሰማራ አድላቢ፡-

## PART THREE

## RIGHTS AND OBLIGATIONS OF MARKET ACTORS

**12. Common Obligations**

Any market actor shall:

1/ not trek for more than 50 kilo meters live animals purchased from first and second level live animal market center or from feedlots;

2/ not trek or transport by means of transportation live animals purchased from first and second level live animal market center or from feedlots for more than 8 hours by vehicle without giving them rest;

3/ provide feed, water and other necessary care to the animals during transportation;

4/ supply to market live animals free from observable damages and diseases;

5/ refrain from any misleading acts during live animal market and health control;

6/ except consumers, receive confirmation from appropriate organ that he correctly transported those animal types and quantity purchased from first and second level live animal market center or from feedlots and that the animals specified in transporting permit reached to the destination within the time and appropriately.

**13. Obligations of Feedlot Operator**

Without prejudice to Article 10 of the Proclamation, any feedlot operator engaged in live animals marketing shall:

፩/ የቁም እንስሳት ከማድለቢያ ጣቢያ ብቻ ለሁለተኛ ደረጃ የቁም እንስሳት ግብይት ማዕከላት የማቅረብ፤

፪/ አግባብነት ካለው አካል ያገኘውን ንግድ ፈቃድ ለሶስተኛ ወገን ያለማስተላለፍ፤

ግዴታዎች አሉበት፡፡

፲፬. <u>የላኪ ግዴታዎች</u>

የአዋጁ አንቀጽ ፲፩ ድንጋጌ እንደተጠበቀ ሆኖ ማንኛውም በቁም እንስሳት ግብይት ላይ የተሰማራ ላኪ፡-

፩/ የኳራንቲን ጊዜያቸውን ያጠናቀቁ የቁም እንስሳትን ብቻ ለውጪ ገበያ የማቅረብ፤

፪/ ወደ ውጭ ሀገር የሚልከውን የቁም እንስሳት በኢትዮጵያ ደረጃ መሰረት ማዘጋጀት ወይም የኢትዮጵያ ደረጃ ያልወጣለት በሆነ ጊዜ በገዢው ፍላጎት መሰረት የማዘጋጀት፤

፫/ በድርጅቱ ውስጥ የሚገኙ ወደ ውጭ ሊላኩ የተዘጋጁ ቁም እንስሳትን በአካል ተገኝቶ ለመቆጣጠር ወይም ስለእንስሳቱ መረጃ ለማግኘት አግባብ ያለው አካል ሲጠይቅ ትብብር የማድረግ፤

፬/ የንግድ ፈቃዱን በማንኛውም ሁኔታ ለሶስተኛ ወገን አሳልፎ ያለመስጠት፤

ግዴታዎች አሉበት፡፡

፲፭. <u>የአጓጓዥ ግዴታዎች</u>

የአዋጁ አንቀጽ ፲፪ ድንጋጌ እንደተጠበቀ ሆኖ በቁም እንስሳት ማጓጓዝ ንግድ የተሰማራ አጓጓዥ የቁም እንስሳቱ በጉዞ ወቅት እንዲያርፉ፣ እንዲመገቡ እና ውኃ እንዲያገኙ እንዲሁም አስፈላጊውን እንክብካቤ እንዲያገኙ የማድረግ ግዴታዎች አሉበት፡፡

1/ supply live animals to second level market center only from feedlot;

2/ not transfer his business licence obtained from appropriate organ to the third parties.

**14. <u>Obligations of Exporter</u>**

Without prejudice to Article 11 of the Proclamation, any exporter engaged in live animal market shall have the following obligations:

1/ to export only those live animals completed their quarantine period;

2/ to prepare exportable live animals based on the Ethiopian standard or if there is no Ethiopian standard, on the basis of the buyer's standard and quality;

3/ to cooperate when requested by the appropriate organ to physically supervise the exportable live animals found within the premises of the enterprise or to provide information about the exportable live animals;

4/ not transfer his business licence obtained from appropriate organ to the third parties.

**15. <u>Obligations of Transporter</u>**

Without prejudice to Article 12 of the Proclamation, a transporter engaged in live animal transport business shall have the obligation to provide rest, feed, water and other necessary care to animals during transportation.

ሂደቶች ሕገወጥ ድርጊት የተፈፀመባቸውን የቁም እንስሳት ወይም የቁም እንስሳት የጫነ ማጓጓዣ ተሽከርካሪ የመያዝ ሥልጣን ይኖረዋል፡፡

፫/ ግብይት ተቆጣጣሪ በዚህ አንቀጽ ከንዑስ አንቀጽ (፩) እና (፪) የተዘረዘሩት ኃላፊነቶችን ሲወጣ አዋጁ፣ ይህ ደንብ ወይም ደንቡን ተከትለው የወጡ መመሪያዎች መጣሳቸውን ሲያረጋግጥ በአስቸኳይ አግባብ ላለው አካል ሪፖርት ማድረግ አለበት፡፡

## ፲፰. ሕገወጥ ድርጊቶችን ስለመጠቆም

፩/ ማንኛውም ሰው አዋጁን፣ ይህን ደንብ ወይም ደንቡን ተከትለው የወጡ መመሪያዎችን በመተላለፍ ሕገወጥ የቁም እንስሳት ማጓጓዝ ወይም ግብይት ተፈጽሟል ወይም ሊፈጸም ነው ብሎ ሲያምን በአካባቢው ለሚገኝ የቁም እንስሳት ግብይት ተቆጣጣሪ ወይም አግባብነት ላለው አካል መጠቆም ይችላል፡፡

፪/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) መሰረት ጥቆማ አቅርቦ ሕገወጥ ድርጊት የተፈጸመበትን የቁም እንስሳ ያስያዘ ማንኛውም ሰው በዚህ ደንብ አንቀጽ ፲፱ (፭) (ለ) መሰረት የጠቋሚ አበል ይከፈለዋል፡፡

፫/ ጠቋሚው በመጠቆሙ ምክንያት ማንኛውም አይነት ጉዳት እንዳይደርስበት ማንነቱ እንዳይገለጽ ይደረጋል፡፡

## ፲፱. ሕገወጥ ድርጊት የተፈጸመበት የቁም እንስሳ ማድለቢያ ወይም ማቆያ ጣቢያ እና የተያዘ የቁም እንስሳ

፩/ በዚህ ደንብ በአንቀጽ ፲፯ (፫) መሠረት የተቆጣጣሪ ሪፖርት ሲደርስ አግባብ ያለው አካል ሕገወጥ ድርጊት የተፈፀመበትን የቁም እንስሳት ማድለቢያ ወይም ማቆያ ጣቢያ ያግዳል፡፡

when illegal acts committed during marketing of animals in the market centers or during transporting or in any other marketing activity;

3/ The market supervisor shall, immediately report to the appropriate body, if he discovers violation of the Proclamation, this Regulation and directive issued hereunder, while discharging his responsibilities specified under sub-article (1) and (2) of this Regulation.

## 18. Informing Illegal Acts

1/ Any person when he believes that illegal marketing of live animal is committed or is going to be committed in violation of the Proclamation, this Regulation or directives issued hereunder may inform same to the local live animal market supervisor or appropriate organ.

2/ Any person who informs illegal marketing committed pursuant to sub-article (1) of this Article and causes seizure of the animals shall be paid the commission fee provided for under Article 19 (5) (b) of this Regulation.

3/ The informants identity shall not be disclosed to protect him from any harm that may be caused due to information he supplied.

## 19. Feedlots or Waiting Centers Involved in Illegal Acts or Live Animal Seized

1/ The appropriate organ shall, upon receiving report in accordance with Article 17 (3) of this Regulation, suspend the live animals feedlot or waiting center involved in illegal live animals marketing.

፪/ በዚህ ደንብ በአንቀጽ ፲፯ (፪) መሠረት የቁም እንስሳት ወይም የቁም እንስሳት የጫነ ማጓጓዣ ተሽከርካሪ የተያዘበት ወይም በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) መሰረት የቁም እንስሳት የማድለቢያ ወይም ማቆያ ጣቢያ የታገደበት ማንኛውም ሰው በአምስት የሥራ ቀናት ውስጥ ተቃውሞውን አግባብነት ላለው አካል ሊያቀርብ ይችላል፡፡

፫/ አግባብ ያለው አካል በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፪) መሠረት የቀረበውን ተቃውሞ ከሰባት ቀን ባልበለጠ ጊዜ ውስጥ መርምሮ ውሳኔ ይሰጣል፣ አግባብ ያለው አካል ውሳኔ፡-

ሀ) የተቆጣጣሪውን እርምጃ የሚሽር ከሆነ ወዲያውኑ የተያዘው ቁም እንስሳ ለአመልካቹ እንዲመለስ ወይም የታገደው ማድለቢያ ወይም ማቆያ ጣቢያ እገዳ እንዲነሳ ይደረጋል፤

ለ) የተቆጣጣሪውን እርምጃ የሚያጸና ከሆነ፡-

(፩) የቁም እንስሳው መወረሱን የሚገልጽ ሕጋዊ ደረሰኝ ለግለሰቡ በመስጠት እንስሳቱ በግልጽ ጨረታ ወይም በግልጽ ጨረታ ካልተሸጠ ለመንግስት ወይም ለግል ተቋማት በድርድር እንዲሸጥ ተደርጎ ገንዘቡ አግባብ ያለው አካል በከፈተው ዝግ የባንክ ሂሳብ ገቢ ይደረጋል፤ ወይም

(፪) የታገደው ማድለቢያ ጣቢያ ባለቤት ወይም ተከራይ ላይ በአዋጁ አንቀጽ ፲፭ (፭) መሠረት አስተዳደራዊ እርምጃ ይወስዳል፡፡

2/ Any person whose live animals or truck loaded with live animal is seized pursuant to Article 17 (2) of this Regulation or live animal feedlot or waiting center is suspended in accordance with sub-article (1) of this Article may lodge petition of objection to appropriate within five working days.

3/ The appropriate organ shall examine and pass decision with seven days on the petition lodged pursuant to sub-article (2) of this Article. If the decision of the appropriate organ:

a) overrules the action taken by the supervisor, the live animal seized shall immediately be returned to the petitioner or the suspension of the feedlot or waiting center shall be lifted; or

b) approves the action of supervisor:

(1) receipt of confiscation shall be issued to the petitioner and the live animals shall be sold in an open auction or otherwise be sold to public or private organization through dealings and the proceed shall be deposited in blocked account opened by the appropriate organ; or

(2) appropriate administrative measure shall, on the owner or renter of the feedlot suspended, be taken pursuant to Article 15 (5) of the Proclamation.

፬/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ ፫ በተመለከተው የጊዜ ገደብ ውስጥ ውሳኔ ያልተሰጠ ከሆነ ወይም በዚሁ ንዑስ አንቀጽ በፊደል ተራ (ለ) መሠረት በተሰጠ ውሳኔ ላይ ቅሬታ ያለው ሰው ውሳኔው በተወሰነ ወይም የጊዜ ገደቡ እንዳለፈ በ፴ ቀናት ውስጥ ጉዳዩን የማየት ስልጣን ላለው ፍርድ ቤት ክስ ማቅረብ ይችላል፡፡

፭/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፬) መሰረት ይግባኝ የቀረበለት ፍርድ ቤት አግባብ ያለው አካል የሰጠውን ውሳኔ፦

ሀ) ከሻረው የቁም እንስሳውን ለመሸጥ የወጣው ወጪ ተቀናሽ ተደርጎ የሽያጩ ገንዘብ ለባለቤቱ ተመላሽ ይደረጋል፣ አስተዳደራዊ መቀጮው እንዲነሳ ይደረጋል፣ ወይም

ለ) ካጸናው ወይም የቁም እንስሳቱ ባለቤት በተወሰነው የጊዜ ገደብ ውስጥ ይግባኝ ካላቀረበ ከቁም እንስሳቱ ሽያጭ ገንዘብ አስተዳደራዊ ወጪዎች ተቀንሰው ፵% ለጠቋሚው ወይም ያለጥቆማ የተያዘ ከሆነ ለያዘው የመንግሥት ፀጥታ ተቋም ይከፈላል፣ ቀሪው ፷% ለመንግስት ገቢ ይደረጋል፡፡

፮/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) መሰረት የታገደ የቁም እንስሳት ማድለቢያ ወይም ማቆያ ጣቢያ ለሌላ የግብይት ተሳታፊ ሊከራይ ይችላል፡፡

## ፳. የቁም እንስሳት ጤና ቁጥጥር

፩/ አግባብ ያለው አካል በአዋጁ አንቀጽ ፯ (፫) መሠረት በቅድመ ግዥ የጤና ምርመራ የጤና ችግር ምልክት የታየባቸውን የቁም እንስሳት በመለየት ህክምና ወይም እንክብካቤ እንዲያገኙ ወይም ሌላ ተገቢ እርምጃ እንዲወሰድባቸው ያደርጋል፡፡

4/ If decision is not rendered in accordance with sub-article (3) of this Article within the specified period or the person aggrieved by the decision passed pursuant to paragraph (b) of sub-article (3) of this Article may institute case in a court of law having jurisdiction within 30 day after the decision is passed or after laps of period specified for decision.

5/ If the court handled the case pursuant to sub-article (4) of this Article:

a) revokes the decision rendered by the appropriate organ, the expense incurred for selling the live animal shall be deducted from the proceed and the reaming amount shall be refunded to owner or lift the administrative measure; or

b) approves the decision or if the owner of the animal fails to take appeal within the specified period, after deduction of the administrative expenses 40% of the proceed shall be paid to the whistle blower as a commission or if there is no whistle blower to the government security organ seized the live animals and the remaining 60% shall be paid to Government.

6/ Feedlot or waiting center suspended in accordance with sub-article (1) of this Article may be leased to another market actor.

## 20. Live Animal Health Control

1/ The appropriate organ shall cause the taking of medical treatment or care or other proper measure on live animals found with the symptom of sickness during pre-marketing health check conducted in accordance with Article 7 (3) of the Proclamation.

፪/ የገበያ ማዕከሉ የእንስሳት ጤና ተቆጣጣሪ የጤና ችግር የሌለባቸውን የቁም እንስሳት ለግብይት እንዲቀርቡ ፈቃድ በመስጠት፣ ግዥና ሽያጭ ከተፈጸመባቸው በኋላ የመለያ ቁጥር፣ የጤና ሰርተፍኬት እና የማጓጓዣ ፈቃድ እንዲያገኙ ይደረጋል፡፡

**፳፩. የጤና ተቆጣጣሪ ባለሙያ ስለመመደብ**

፩/ የግብርና ሚኒስቴር ወይም የክልል ግብርና ቢሮዎች የቁም እንስሳት ጤና ተቆጣጣሪዎችን ይመድባሉ፡፡

፪/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) መሰረት የሚመደብ የቁም እንስሳት የጤና ተቆጣጣሪ በመስኩ በቂ ዕውቀትና መልካም ሥነ ምግባር ያለው መሆን ይኖርበታል::

**፳፪. የቁም እንስሳት ጤና ተቆጣጣሪ ኃላፊነት**

፩/ የቁም እንስሳት ጤና ተቆጣጣሪ፡-

ሀ) ከመጀመሪያና ከሁለተኛ ደረጃ የቁም እንስሳት የግብይት ማዕከላት ተገዝተው ወደ ማድለቢያ ጣቢያ እና ወደ ኤክስፖርት ቄራ የሚጓጓዙ የቁም እንስሳት ጤና ቁጥጥርን በተመለከተ ግብርና ሚኒስቴር ስለ ቅድመ ግዢ ምርመራ የሚያወጣቸውን መመሪያዎች መከበራቸውን፣

ለ) በመጀመሪያና በሁለተኛ ደረጃ የግብይት ማዕከላት እና በማጓጓዝ ሂደት የሚታየውን የቁም እንስሳት ጤንነት ሁኔታ፣ እና

ሐ) በቁም እንስሳት አድላቢዎችና ላኪዎች የሚከናወነውን የቁም እንስሳት የጤና አጠባበቅ ዝግጅት፣

የመቆጣጠር እና የማረጋገጥ ኃላፊነት ይኖረዋል፡፡

2/ The live animal health controller of the market center shall approve those animals found health so as to be supplied to market and after being marketed issue them code, health certificate and transporting permit.

**21. Assigning Health Supervising Professional**

1/ The Ministry of Agriculture or regional agriculture bureaus shall assign live animal health supervising professional.

2/ A live animal health controlling professional assigned in accordance with sub-article (1) of this Article shall have knowledge in the field and good ethical background.

**22. Responsibilities of Live Animal Market Health Supervisor**

1/ Live animals health controller shall have the responsibilities to control and ensure:

a) the observance of directives issued by the Ministry of Agriculture with respect to pre-purchase health diagnosis for live animals to be transported to feedlot and export abattoirs after being purchased from first and second level live animal market centers;

b) health of live animals marketed first and second level live animal market centers and during transporting them;

c) live animals health care process performed by live animals feedlot operators and exporters.

፪/ የቁም እንስሳት ጤና ተቆጣጣሪ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) የተመለከተውን ኃላፊነቱን ለመወጣት ወደ ማንኛውም የቁም እንስሳት ማድለቢያ ወይም የገበያ ማዕከላት በሥራ ሰዓት ለመግባት፣ ያላቸውን ሰነዶች ለመመልከትና አስፈላጊ መረጃዎችን የማጣራት ሥልጣን ይኖረዋል፡፡

## ክፍል አምስት
## ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች

፳፫. የመተባበር ግዴታ

የግብይት ተቆጣጣሪዎች ይህንን ደንብ ተግባራዊ ለማድረግ ለሚያደርጉት እንቅስቃሴ ማንኛውም ሰው የመተባበር ግዴታ አለበት፡፡

፳፬. ተፈጻሚነት ስለማይኖራቸው ደንቦችና መመሪያዎች

ይህን ደንብ የሚቃረን ማንኛውም ደንብ፣ መመሪያ ወይም ልማድ በዚህ ደንብ በተሸፈኑ ጉዳዮች ላይ ተፈጻሚነት አይኖረውም፡፡

፳፭. ደንቡ የሚጸናበት ጊዜ

ይህ ደንብ በፌዴራል ነጋሪት ጋዜጣ ታትሞ ከወጣበት ቀን ጀምሮ የጸና ይሆናል፡፡

አዲስ አበባ የካቲት ፲ ቀን ፪ሺ፯ ዓ.ም

ኃይለማርያም ደሳለኝ

የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ጠቅላይ ሚኒስትር

2/ The live animals health supervising officer shall, in order to discharge the responsibility specified under sub-article (1) of this Article, have the responsibility to enter any feedlot operating premises, market centers at official working hours and to observe documents and examine whenever necessary.

## PART FIVE
## MISCELLANEUOS PROVISIONS

23. **Duty to Cooperate**

Any person shall have obligation to cooperate with the market supervisor for the implementation of this Regulation.

24. **Inapplicable Regulations and Directives**

No regulations, directives or practice shall, in so far as they are inconsistent with this Regulation, have effect with respect to matters provided for by this Regulation.

25. **Effective date of the regulation**

This Regulation shall enter into force on the date of publication in the Federal Negarit Gazette.

**Done at Addis Ababa, this 17th day of February, 2015.**

**HAILEMARIAM DESSALEGN**

**PRIME MINISTER OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA**

ብርሃንና ሰላም ማተሚያ ድርጅት